# ጦቢያ

ቅጽ 3 ቁጥር 3 1987

## መጪው ጊዜ




- ያቆጠቆጠው ራዕይ (ልጅ ሚካኤል አምሩ)
- መንግሥት ከደም ሥር ሲገባ (ስንሻው)
- መከላከያ ሠራዊቱ ለምን ወደቀ?
- መኢሶን ተሸንፏል? ከኢሕአፓ በምን ይለያል? (ዶ/ር ነገደ ጎበዜ)
- የተማሪ እንቅስቃሴ አሻራና የፖለቲካ ባህላችን (መሸሻ ብሩ)
- እንደዶርዜ እህቶቼ (የአሰፋ ጫቦ ቀለጣፋ ወግ)
- ሰው ስንፈልግ ባጀን (ጸ.ገ.መ.አ.)
- ከአባይ ማስታወሻዬ
- አስጨናቂው ፖሊሲ

## ያለፈውና መጭው ትግል በውስጥ አዋቂ ዓይን

# መኢሶን ተሸነፈስ? ከኢሕአፓ በምን ይለያል?

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ
(የመጨረሻው ክፍል)

መኢሶንን ሙሉ በሙሉ ተሸንፏል ወይ? ሰማይ ወጥተን መሬት ገብተን ለሥልጣን እንብቃ የሚል ትግል አካሂደን ቢሆን ኖሮ ሙሉ በሙሉ ተሸንፈናል ማለት ይቻላል:: መሬት ላራሹ፣ ዲሞክራሲ፣ በብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነት የተገነባች ኢትዮጵያ ብለን ነው የተነሳነው:: ለኛ የኢትዮጵያ አብዮት ቁልፍ ጥያቄ ነበር ገፌኛ ሥርዓትና የለውጥን ርምጃ አፍኖ የያዘ ስለነበረ:: ከሕዝቡ 90 በመቶ በላይ ኑሮ በመሬት ጥያቄ ላይ የተንጠለጠለ ስለነበረ:: የመሬቱ ስሪት ለብሄሮች ጭቆና የኢኪኖሚ ጉዝጓዝ ስለነበረና የዚህ ጭቆና ምልክትም ስለነበረ:: መኢሶን ከደርግ አንጻር «ሂሳዊ ድጋፍ» የሚለውን አቋም የያዘው ከመጀመሪያው አልነበረም:: እርግጥ በውጭ የነበርነው ይህ አቋም ነበረን:: ድርጅቱ ግን ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ይህንን አቋም የያዘው ከመሬት አዋጅ በኋላ ነው:: ማለትም ከየካቲት 1967 ዓ.ም በኋላ:: የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት እንዲቋቋም የገፋውና እዚህ ጽ/ቤት ውስጥ በሰፊው የተሳተፈው በዚህ ሳቢያ በከተሞች ከደርግ ሥልጣን ለመካፈል አልነበረም:: በዚህ ተቋም አማካኝነት በመንግሥት የተደገፈና የሚረዳ ሥራ በገጠር ለመስራት ነበር::

የሆነውም ይኸው ነው:: ሕዝብ ድርጅት ሲቋቋም የኛ የዘመቻው መቀጠል ነበር:: በገጠር በ1968 እና በ1969 ዓ.ም የኛ ታጋዮች ያካሄዱት ትግልና የተዋጓቸው ኃይሎች እነዛው ዘመቻውን ሲዋጉ የነበሩ ኃይሎች ናቸው:: ለዚህ ትግል ከሕዝብ ድርጅት አባላት ከ80 ከመቶ በላይ የሚሆኑትን በገጠር ከገበሬው ጐን አሰልፈናል:: በነዚህም ኃይሎች አማካኝነት በየከፍለ ሃገሩ በሺህ የሚቆጠሩ የገበሬ መሪዎች በመኢሶን ባንዲራ ሥር አሰልፈን ታግለናል:: የኛ አባላትና ደጋፊዎች ከገበሬዎች ጐን ተሰለፈው ያደረጉት መስዋዕትነት ፍሬ ቢስ አልነበረም:: የፊውዳሊዝም ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ከሃገራችን በየመንደሩ በገበሬዎች ትግል ሲደመሰስ የመኢሶን ታጋዮች ከገበሬው ጐን ቆመው እየተሰው ነበር:: በነዚህ ሰማዕታት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች ደህንነት በደማቸው በከፈሉት ጓዶች አስተዋጽኦ የሚሰማንን ኩራት ማንም ምን ጊዜም ሊነጥቀን አይችልም:: ያኔ ከአገራችን የፊውዳሊዝም ቀንበር ሲደመሰሰስ እኛም ነበርንበት እንላለን:: ምናልባት እንደ ፖለቲካ ድርጅት ለፊውዳሊዝም መደምሰስ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በአካል ተገኝቶ ከሁሉም ድርጅቶች ይበልጥ አስተዋጽኦ ያደረገ ድርጅት ቢኖር መኢሶን ነው ለማለት እደፍራለሁ::

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች አምነውበት የተሰለፉበት አብዮት ሙሉ በሙሉ ግቡን አልመታም እንጂ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኗል አልልም:: ከዚህም አልፌ እሄዳለሁ:: የፊውዳሊዝም መደምሰስ ብቻ አይደለም:: በዚህ ምክንያት ሌሎቹም ያልተሟሉት የየካቲት አብዮት ጥያቄዎች እንዲፈቱ መንገድ ከፍቷል:: ለታህሣሱ ጉባኤ በቀረበው መንደርደሪያ ሰነድ ላይ ይህ ጉዳይ በግልጽ ተቀምጧል:: አብዮታዊ ትግላችን ሙሉ በሙሉ ፍሬ ቢስ አልነበረም:: የቀድሞው የመሬት ስሪት መወገድ የብሄሮችን ጥያቄ በውይይትና በዲሞክራሲ ለመፍታት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ብለን አስቀምጠነዋል::

በዚህ አመቺ ሁኔታ ተጠቅሞ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ደህንነት በጋራና በውይይት ይህንን ጥያቄ መፍታት የዛሬ ፖለቲካ ታጋዮች አንዱ ትልቅ አደራ ነው:: ከሁሉም ወገን መልካም ፈቃድ ካለ በግማሽ ተሰናከሉ ቢቀርም ያ አብዮት በዚህ በብሄሮች ጥያቄ አንጻር አመቻችቶልን የሄደው የእኩልነት፣ የወንድማማችነት ጉዝጓዝ አለ:: ሌላም በዛሬው ግርግርና የብሄር/ ብሄረሰብ ድርጅቶች ማየል የተነሳ ብዙ ሰው ልብ የማይለው ቁም ነገርና እኛ መኢሶኖች የቀሰምነው ትምህርት አለ:: መሬት ላራሹ ብለን ያኔ ስንዋደቅ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝቦች ደህንነት በአንድ ላይ ታግለን ነው:: የደርግ መንግሥት የመኢሶን ቀንደኛ መሪዎች ብሎ በአንድ ቀን አምስት ታጋዮቻችንን ማለትም ኃይሌ ፊዳን፣ ዶክተር ንግሥት አዳነን፣ ቀንጂት ከበደን፣ደስታ ታደሰንና ኃይሉ ገርባባን ወስዶ ሲረሽን እነዚህ መሪዎቻችን ከኦሮሞ፣ ከትግራይ፣ ከአማራና ከጉራጌ ብሄረሰብ የተውጣጡ ዜጎች ነበሩ:: ለዚህ ወይም ለዚያ ብሄር ሳንል በአንድ መንፈስ፣ በአንድ ዓላማ በወንድማማችነት መንፈስ ታግለናል:: ፊውዳሊዝምን የመደምሰስ ያህል ቁም ነገር የተሠራው በዚህ ወይም በዚያ ብሄር ስም በተደራጁ ኃይሎች ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ጥቅም፣ ለእኩልነታቸውና ለጋራ ብልጽግናቸው አብረው በተሰውት ጓዶቻችን ትግልም ነው:: ለኔ አብዮቱ ትቶልኝ ያለፈው አንድ ትምህርት ይኸ ነው:: ለዚህ ነው ለምሳሌ ምን ቢመጣ አማራ እንደመሆኔ መጠን የአማራ ድርጅት አባል ለመሆን እንኳን በውኔ በህልሜም የማይመጣብኝም:: ይህ ማለት ግን በብሄር መደራጀትን መቃወም አይደለም:: ይሁንና በብሔር/ብሔረሰብ መደራጀት አሉታዊ ልምድ አለው:: እሱን አሽቀንጥረን እንጣለው፣ እንመርምረው፣ ትምህርት እንቅሰምበት ለማለት ያህል ነው::

የተሰናከለው አብዮት በዚህ በብሄሮች ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በዚያም

ባልተሳካለት የዲሞክራሲ ጥቁም ላይ የማይናቅ ትምህርት ትቶ ነው ያለፈው:: ዛሬ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ያስፈልጋል ብቻ ሳይሆን ይቻላል የምንለው በዚህም ጥያቄ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ደግሞ ገበሬው«አይቶ የተነሳው» እጁን ካስገባ በኀላ የተነጠቀው የራሱን ጉዳይ በራሱ የማስተዳደር ልምድ በአበዮቱ መጀመሪያ አመታት አግኝቶ ስለነበረ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዛሬ ዲሞክራሲ ብንላቸው ተጨባጭ ነገር ነው ለነሱ:: ለአጭር ጊዜም ቢሆን የዲሞክራሲን ጸጋ ቀምሰነዋልና:: ይህንን ከተነጠቁ በኋላ ደግሞ በከፈሉት የገፍ ግድያ፣ የገፍ ረሃብ፣ የገፍ ስደት መከራ ጸረ ዲሞክራሲ ማለት ምን እንደሆነ በተጨባጭ ያዩትና አሁንም የሚያዩት ሃቅ ነውና::

ሙሉ በሙሉ አልተሸነፍንም ስል ራሴን ለማጽናናት ሳይሆን በዚህ በአብዮቱ ትግልና ባስከተለው መስዋዕትነት ሳቢያ የመሬቱን ስራት ደምስሰናል፣ በዚህም የተነሳ ለቀሩት ቁልፍ ጥያቄዎች ማለትም ለብሄሮች ጥያቄና ለዲሞክራሲ ጥያቄ መፈታት የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል ለማለት ነው::

ግን ደግሞ ሽንፈት የለም ማለት አይደለም:: ትውልዳችን ከሰላሳ ዓመት ጀምሮ ያነሳውና የተዋደቀለት የእኩልነት፣ የነጻነት፣ የብልጽግናና የፍትህ ዓላማ እጃችን መግባት ከጀመረ በኋላ አምልጦልናል:: እንዲያውም ይህንን ሽንፈት የጉላ የሚያደርገውና ይበልጥ እንዲሰማን የሚያደርገው ከማይናቁ ታሪካዊ ድሎች በኋላ የደረሰ ክስተት መሆኑ ነው:: የኛ ትውልድ መሬት ላራሹ ብሎ ሲነሳ ይህንን ከሥራ ላይ ለማዋል እንደቀደሙት አብዮቶች፣ በባሌም በቦሌም እየገባን፣ የሃያም የሰላሳም ዓመታት ረዥም ትግልን አድርገን የምናመጣው ነገር አርገን ነበር የምንጠብቀው:: ሃያና ሰላሳ ዓመታት እኛና የኢትዮጵያ ጤሰኞች በሕገወጥነት የምንታገልበት:: ፊውዳሎቹ ደግሞ በህግና በመንግሥት በኩል ሆነው የተከላከሉበት ረዥም ትግል ነበር የጠበቅነው:: ይህ አብዮታዊ ትውልድ ከተጸነሰበት ከተማሪ ንቅናቄ በወጉ ገና ሳይላቀቅ አብዩቱ ደረሰበት::

በመሬት ላራሹ ጥያቄ ምላሽ ህጋዊ ፊውዳሎቹ ህገወጥ የሚሆኑበት ሁኔታ ተፈጠረ:: ብዙ ድሎች ተገኙ:: ከነዚህ አብዛኞቹ መልሰው ተነጠቁ:: እነዚህ ድሎች እንዲገኙ ብዙ ደምና እንባ ፈሰሰ:: እንዳይነጠቁም እንዲሁ ብዙ ደምና እንባ ፈሰሰ:: ስለዚህ ነው ሽንፈት አለ ብቻ ሳይሆን በጣም የሚያንገበግበን ሽንፈት ነው የምለው::

ይህ ሽንፈት እንዲደርስ ያደረጉት ብዙ ስህተቶች ናቸው:: አንዳንዶቹን ልናመልጣቸው እንችል እንደነበረ እጠራጠራለሁ:: ያኔ በነበረው አነጋገር አብዮት የመጣላቸውና አብዮት የመጣባቸው እንል ነበር፣ እኛን ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር ከመጀመሪያው ከፍል ያለአንዳች ማመንታት እያካተትን:: አንዳንዴ ሳስበው ግን ይኸ አብዮት እዛ ታጋይ ትውልድ ላይ «አልደረሰበትም ወይ?» እያልኩ እጠይቃለሁ:: ለሃገር ፍቅርና ለሕዝብ ለመሰዋት ካለው የጋለ ስሜት በስተቀር የትኛው ድርጅታዊ አቅሙ፣ የትኛው የአብዮታዊ ትግል ልምዱ፣ የትኛው ዘወር ብሎ የሚያየውና የሚመካበት የማህበራዊ ለውጥ የትግል ቅርስ ነበር እንዲህ ዓይነቱን መሬት አንቀጥቅጥ የለውጥ ሂደት ለመምራት ብቁ የሚያደርጉት? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ:: ለዚህ ነው ይህ አብዮት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጣለት እንጂ እኛስ ገና በቅጡ ሳንደራጅ ነው የደረሰብን ለማለት የምደፍረው:: ሁሉም ሰው የሚለው ነገር አለ:: አብዮቱ በግብታዊነት ነው የፈነዳው:: አመራሩም እስከተወሰነ ደረጃም ቢሆን ግብታዊ ነበር ማለት ይቻላል:: ትዝ ይለኛል አንድ ጊዜ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት «ለመሆኑ ይህንን አብዮት የሚመራው ማነው»? የሚል ከባድ የንድፈ ሃሳብ (ቲዎሪ) ጥያቄ ተነስቶ አንድ ጧት ሙሉ ክርክር ሲካድ:: ወዛደሩ? ንዑስ ከበርቴው? የንዑስ ከበርቴው ግራ ክንፍ? . . . . ጥያቄው በቅጡ ሳይመለስ ለምሳ ልንበተን ስንል ጧቱን ሙሉ ዝም ብየ ስታዘብ ከውይይቱ አለመሳተፌን የተመለከተ ዶ/ር ሰናይ «ነገደ! ምነው ዝም አልክ? ያንተስ አስተያየት ምንድነው፣ ይህንን አብዮት ማነው የሚመራው?» ብሎ ቢጠይቀኝ «ዝም ብላችሁ ነው እኮ የምትለፉት:: ይህ አብዮት መሪ አለው ማለት አልች ልም:: አድሃሪዎች ከኋላችን እያባረሩን እኮ ነው ከፊት ከፊት የምንሮጠው::»ብየ ስመልስ:: እርግጥ የተጋነነ አባባል ነው:: ግን ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙም እሩቅ አልነበረም:: እንግዲህ በዚህ ባልተ ዘጋጀንበት ሁኔታ፣ በዚያ ነገሮች በአስደ ናቂ ፍጥነት በሚቀያየሩበት ማዕበል ውስ ጥ እየተዋከብን እያለን ብዙ ከባድ ስህተ ቶች ማድረጋችን ልናመልጥ የማንችለው የታሪክ እጣ ነበር ማለት እደፍራለሁ::

ይህንን የምለው ከኃላፊነት ለማምለጥ አይደለም:: መኢሶን ያን ጊዜ ለደረሰው ሽንፈት የተጠያቂነት ድርሻ አለው:: በተከፈለው መስዋዕትነትና በተገኘው ድል ብቻ አይኩራራም:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች አምነውት ከሥሩ ተሰልፈው፣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወዛደሮች «ድርጅታችን፣ መሪያችን» ብለውት፣ አርማውን አንስተው፣ በሺ የሚቆጠሩ ወጣት አብዮታውያን አመራሩን ተቀብለው፣ ይህንን ሁሉ ኃይል አሰልፎ እያለ መርቶ ለሙሉ ድል አለመብቃቱ ለዚህ የህዝብ ድጋፍና አመኔታ ተመጣጣኝ የሆነ የፖለቲካ ብስለትና ድርጅታዊ ብቃት እንዳልነበረው ለኔም ለመኢሶን አባላትም ግልጽ ነገር ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ በኛና ከኛ ውጭ ሆነው መኢሶንን በሚተቹ ሰዎች መሃከል መሠረታዊ ልዩነት አለ::

አንዳንድ ድርጅቶችም ጋር ሆነ ግለሰቦች ጋር ስንወያይ ሂስ አርጉ ሲሉን እነሱ ከኛ የሚጠብቁት በአብዮቱ ዘመን የተከተልነውን የፖለቲካ መስመር ስሁተት ነበር እንድንልላቸው ነው:: ለ20 ወራት ያህል ከደርግ ጋር አብረን መስራታችንን፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚለውን ጥያቄ መቃወማችንን፣ ዘመቻው እንዲቀጥል እንጂ እንዳይቋረጥ መታገላችንን፣ ከኢትዮጵያ ገበሬዎች ጉን ለመሰለፍና ለመዋደቅ በር የከፈተልንን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ማቋቋማችንን፣ ከደርግ ጋር አብረን በመሥራታችን ብቻ ሳይሆን በኋላ ደግሞ ነሐሴ 1969 ላይ ማቋረጣችንን ... እነዚህና ሌሎች ዋና ዋና የሆኑት መኢሶን የተከተላ ቸው የፖለቲካ አቋሞች ምን ጊዜም ስህተት ናቸው ወይም ነበሩ እንልም::

እንዲያውም እኛ የምንለው ፖለቲካችን ስህተት ነበር ሳይሆን ይህንን ሥራ ላይ ለማዋል ብቃት ያለው ድርጅ ታዊ አሠራርና አቅጣጫ አልነበርንም ነው:: ከዚህ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ይህንን የፖለቲካ መስመር ሥራ ላይ ለማዋል ያኔ በቂ የፖለቲካ ታክቲክ ብስለት አልነበ ረንም እንላለን:: ለደረሰው ሽንፈት የመኢ ሶን የተጠያቂነት ድርሻ የሚፈልቀው ከነዚህ ከተያያዙ ስህተቶች ነው::

በድርጅታዊ አሠራርና አቅጣጫ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ስህተቶችና ዝርክርክነቶች ነበሩብን:: አንዳንዴ ሳስበው አደረጃጀታችን መጽሐፉ እንደሚያዘው አልነበረም ወይ እላለሁ:: «በወዛደሩ መሪነት በአርሶ አደሩ ተባባሪነት . . .» ተባለ:: እዚህ ላይ እጅግ ከማተኮራችን የተነሳ የአደረጃጀት አቅጣጫችን ከሁለት አንጻር የተዛባ ነበር:: አንደኛው ጂኦግራፊን ይመለከታል:: የኢትዮጵያን ፊውዳሊዝም በአገር አቀፍ ደረጃ ለመዋጋት ታጋዮችን በአገር አቀፍ ደረጃ በየአውራጃው፣ በየወረዳው፣ በየመንደሩ መሠማራት አለባቸው ብለን ሃገሪቱን «ለማልበስ» ኃይላችንን በያለበት በታተንን:: ለተከታዩና ቀድሞውንም እንደማይቀር ላወቅነው ከደርግ ጋር ለሚካሄደው ፍልሚያ አንዳንድ

አካባቢዎች ላይ ማተኮር አለብን ብለን የተገነዘብነውና በዚህ አቅጣጫ ቦታና ክፍለ ሃገር እየመረጥን ልዩ ትኩረት መስጠት የጀመርነው ዘግይተን ነበር።

ሁለተኛው መዛባት ከህብረተሰብ ክፍሎች አንጻር ባለን አመለካከት ነበር። ወዛደሩና በተለይም ደግሞ ገበሬው ላይ ማተኮራችን ሳይከፋ ለሌሎች ክፍሎች እምብዛም ደንታ አልነበረንም። የከተማውን ንዑስ ከበርቴ፣ ነጋዴውን፣ የመንግሥት ሠራተኛውን፣ ብሄራዊ ከበርቴውን፣ ወታደሩን . . . ይህን ሁሉ ክፍል ለማደራጀት በቂ ጥረት አላደረግንም። በእምነትና በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይህንን ሁሉ ኃይል ማሰባሰብ ያስፈልጋል እያልን ግን መለፈፋችን አልቀረም። በተለይ በ1967 እና 1968 ዓ.ም ይወጡ የነበሩትን የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥሮች ማየት ነው። ግን ይህንን በተግባር ማዋል ትተን አንዳንዴ የምናካሂዳቸው ቅስቀሳዎች «ግራ ቀደም» ነበሩ። ይህ ደግሞ እነዚህ ክፍሎች መኢሶንን በጥርጣሬ ዓይን ብቻ ሳይሆን በጥላቻም ዓይን እንዲመለከቱት አረጋቸው። ለአብዮቱ ሊሰለፉ የሚችሉትን ኃይሎች በሙሉ ማሰለፉ ቀርቶ አቃታቸው። ይህ ደግሞ ለደረሰው ሽንፈት የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የፖለቲካ ብስለት ማነስ የምለው ይህንን ነው። መኢሶን ግንባር ቀደም ድርጅት ነኝ ካለ አይቀር እነዚህንም ኃይሎች አረጋግቶ፣ ጥቅማቸውን አረጋግጦ መያዝ ነበረበት።

ይህ መዛባትና በከተሞች ያሉትን ኃይሎች ችላ የማለት አዝማሚያ ደግሞ ዝም ብሎ ከሰማይ የወረደ ነገር አልነበረም። መኢሶን ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ምንነትና በዚህ አብዮት መፈታት ስለነበረበት መሠረታ ቅራኔ ከነበረው ትንተና የፈለቀ ይመስለኛል። ደጋግመን እንለው የነበረና ኃይሌ ፊዳ በትክክል በጽሁፍ ያስቀመጡው አቋም ነበረን። የኢትዮጵያ አብዮት ዋናና ቁልፍ ጥያቄ የመሬት ጥያቄ ነው። ዋናና ቁልፍ ቅራኔ በጢሰኛና ባለርስት መሃከል ያለው ቅራኔ ነው። በዚህም የተነሳ ዋናው የአብዮቱ ኃይል ገበሬው፣ ዋና የአብዮታዊው ትግል መፋለሚያ መድረክ ገጠሩ ነው የሚል አቋም ነበረን። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኃይሌ በትክክል እንዳስቀመጠው በከተሞች የነበረው ቅራኔ በወዝአደሩና በከበርቴው መሃከል የነበረው ቅራኔ ነው። በዚህም የተነሳ ዋናው የአብዮቱ ኃይል ገበሬው፣ ዋናው የአብዮታዊው ትግል መፋለሚያ መድረክ ገጠሩ ነው የሚል አቋም ነበረን። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኃይሌ በትክክል እንዳስቀመጠው በከተሞች የነበረው ቅራኔ ነው። በወዝአደሩና በከበርቴው መሃከል የነበረው ቅራኔ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ቅራኔ ነበር እንላለን። ለዚህ ነው ይህንን ዋና ጥያቄ ለመፍታትና ጸረ ፊውዳሉን ትግል ለማራመድ እየወላወለም ቢሆን የመሬት አዋጅን ካወጀውና በዚህ ምክንያት ከባለመሬቶች ጋር ቅራኔ ውስጥ ከወደቀው ከደርግ ጋር ተባብሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን አምነን የገባንበት ነው። የኢህአፓ አስተሳሰብ የኛ ተቃራኒ ነበር። እኛ ገጠሩን የአብዮታዊው ትግል እምብርት አርገን በመውሰዳችን ለምሳሌ ዘመቻው እንዲቀጥል እንታገል ነበር። ኢህአፓ ደግሞ ደጋግሞ እንደጻፈው የአብዮታዊው ትግል «እምብርት» ከተማ ነው ብሎ የሚከራከር ኃይል ነበር። ዘማቾችም ገጠሩን ለቀው ወደ ከተማ እንዲመለሱና ትግሉን እንዲያፋፍሙ ደጋግሞ ጥሪ ያደረገው ከዚህ አቋሙ ተነስቶ ነበር። የሆነ ሆኖ እኛ ከተሞችንና የከተማ ኃይሎችን ችላ እንድንልና በዚህም የፖለቲካ ስህተት እንድናደርግ የገፋፋን ትንተና ይህ ገጠርን እንደ አብዮቱ እምብርት አድርጐ የመውሰዱ አቋም ሲሆን በገጠርና በከተሞች ላይ ሚዛናዊ የሆነ ትከረት እንዳናደርግ የገፋን ይመስለኛል።

ይህ የአደረጃጀት ስልት ጉድለትና በከተሞችና በገጠር ሚዛናዊ ትኩረት ያለመስጠት ችግራችን ብቻውን ሽንፈት አላመጣም። ሌሎች ስህተቶች ባይጨመሩባቸው ኖሮና ገበሬውንና ወዛደሩን እንዳደራጀን ሁሉ አብዮቱ ችግር ሲገጥመው ብቁ የሆነ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራር መስጠት ብንችል ኖሮ የደርሰውን ጉዳት መቀነስ ይቻል ነበር። ግን ደግሞ እዚህ ላይ ዘርዝሬ የማልዘልቃቸው የአደረጃጀት ስህተቶች ፈጽመናል።

ሌላው ጉድለት የፖለቲካ ታክቲክ ብስለት ማጣት ነበር። ደጋግመው ብዙ ጓዶች የሚሉት ነው። እንዲያው በደፈናው የአብዮት «ቦይስካውቶች» ነበርን ማለት ይቻላል። ትግላችን በመላ ሃገሪቱ ላይ ታች እያልን ሕዝቡን ለማስተማር፣ ለማደራጀት፣ ለማስታጠቅ፡ ታግሎና አታግሎ ለሥልጣን ማብቃት ነበር። ይህ መቸም ጥሩ አባባል ነው። ግን በኋላ ሳየው ከአንድ የተወሰነ የመንቃት፣ የመደራጀትና የሕዝብ መታጠቅ ደረጃ ከተደረሰ በኋላ በሕዝብ ስም ሥልጣን ይዘን አብዮቱን ከጥፋት የምናድንበት ደረጃ በፖለቲካ የዋህነት አላመለጠንም ወይ? ህቡእ ልንገባ ሰሞን አንዳንድ ከኛ ቅርብ የነበሩ መኰንኖች «ነገሩ ሁሉ እየተበላሸ ነው። እነዚህ ሰዎች መገልበጥ አለባቸው። ኩዴታ ማድረግ ያስፈልጋል። ይቻላል።» ብለው ለመኢሶን አመራር እቅድ አቅርበው ነበር። «በሕዝብ ትግል እንጂ በኩዴታ አናምናንም።» የሚል መልስ ነው የተሰጣቸው። ያኔ አዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ የታጠቁ ገበሬ ማህበራት በኛ ሥር ነበሩ። የሸዋ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ መኰንን ጆቴ ነበር። በየክፍለሃገሩ ገና በደርግ ቁጥጥር ሥር ያልወደቁ በሺህ የሚቆጠሩ የገበሬ ሚሊሽያዎች በኛ ሥር ነበሩ። ትዝ ይለኛል ከፋ ክፍለ ሃገር ብቻ 20 ሺ አባላት ያለው ሚሊሽያ ተደራጅቶ ዩኒፎርም ሲያሰፋ የመኢሶን አርማ ተጨምሮበትና በዚያ ሰልፍ አሳይቶ በኛና በነፍቅረሥላሴ መሃል ከፍተኛ ግጭት ሲፈጠር፣ ከሃገር ልወጣ ጥቂት ቀናት እንደቀረኝ። በርግጥም በዚያን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ርምጃ ለመሳካት እድል ነበረው።

እንዲህ ዓይነቶቹ የፖለቲካ ታክቲክ ስህተቶች በጣም ብዙ ናቸው። እነዚህንም እዚህ ላይ መዘርዘሩ ለጊዜው አስፈላጊ አይመስለኝም። ወደፊት የመኢሶን ታሪክ ይፋ ሲወጣ ሕዝቡ ይገነዘባቸዋል። እኛ በበኩላችን ግን በየአጋጣሚው በቃል ውይይትም፣ በክርክርም፣ በውስጥ ጽሁፎችም፣ አውጥተን አውርደን ተንትነናቸዋል። ዛሬ በምንም ዓይነት የማንሠራቸው ስህተቶች መዝግበናል፣፣ ከዚህ ሁሉ ትምህርት ቀስመናል። የፖለቲካ የዋሆች ነበርንና አሁን ደግሞ የአራዳ ጮሌዎች እንሁን የሚል ትምህርት አይደለም የምንለው ።።እነዛ አምነውን በኛ ሥር የተሰለፉት በሚሊዮን የሚቆጠሩት ዜጐች ከኛ ጋር የተሰለፉት መኢሶን ጥቅማቸውን የሚያንጸባርቅ፣ ህልማቸውን እውን ሊያደርግ የሚችል፣ የፖለቲካ አቋም ይዞ በመንቀሳቀሱና ለህዝብና ለሃገር ያለውን ፍቅር ከጐናቸው ሆኖ በመሰዋት ስላረጋገጠላቸው ነበር። አሁንም ቢሆን እኛ መኢሶኖች ለሥልጣን ተስገብግበን ይህንን የህዝብ አመኔታ የሚበርዝ አቋም አይኖረንም። የቀሰምነው ትምህርት ቢኖር ለዚህ የህዝብና የሃገር ፍቅራችን ተመጣጣኝ የሚሆን ድርጅታዊ አሠራር፣ ይህንን ህዝባዊ አቋምና ፖለቲካ ከሥራ ላይ ለማዋል ከሚፈልጉ ሁሉ ጋር ተባብረን ለሃገራችን አንድ ቁም ነገር የሚያስገኝ ሥራ ለመስራት የሚያስችለን የፖለቲካ ታክቲክ መቀየስ እንዳለብን ነው። ይህንን ደግሞ ባለን አቅም በሥራ ለማዋል ትግሉን እንቀጥላለን።